# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 81 ህዳር 24 2002 ዓ.ም


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

*ሥራ ለማግኘት፤ አለቃ ለመሆን፤ ጨረታ ለማሸነፍ፤ የነፃ ትምህርት ዕድል ለማግኘት፤ ቁልፍ በሆኑ ዘርፎች የንግድ ፈቃድ ለማግኘትና በአጠቃላይ ሰዉ ሆኖ ለመኖር- ኢትዮጵያዉያን ወይ መለስ ዜናዊ "ወርቃማዉ ዘር" እያለ ከሚጠራዉ ዘር መወለድ አለባቸዉ፤ አለዚያም ሂሊናቸዉን ሸጠዉና "ወይን ለመኖርን" ተከትለዉ የወያኔ ታማኝ አገልጋይ መሆን አለባቸዉ።*

. . . ዝርዘሩን ገጽ 3

## የአዲስ ነገር ጋዜጣ አዘጋጆች ከወያኔ የሚደርስባቸውን ጥቃት በመሸሽ አገር ጥለው እንደተሰደዱ ታወቀ

በአንባቢያን ዘንድ በአጭር ጊዜ ውስጥ እውቅናን ያተረፈ እና በከፍተኛ ቁጥር በኢትዮጵያ ውስጥ ይከፋፈል የነበረ አዲስ ነገር ጋዜጣ ካለፈው ቅዳሜ ጀምሮ አንደተዘጋና ፤ አዘጋጆቹም አገር ጥለው ለመሰደድ እንደበቁ ለማወቅ ተችሎአል።

ከተመሰረተ ጀምሮ በገዢው ፓርቲ አይን ውስጥ የገባው አዲስ ነገር ጋዜጣ፣ ከወያኔ የሚሰነዘሩ "የበሬ ወለደ" ክሶችን ሲቀበል የቆየ ሲሆን፤ የተወሰኑት ጋዜጠኞችም በዚህና በዚያ የሃሰት ክስ ተከሰው ወደ ወያኔ ፍርድ ቤት ሲመላለሱ መቆየታቸው ይታወሳል። የጋዜጣው አዘጋጅ አቶ ታምራት ነገራ እና ባልደረባው ጋዜጠኞ አብረሃም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በፓትሪያርክ ነኝ ባዩ የወያኔ አገልጋይ አባ ጳውሎስ አሳሳቢነት በስም ማጥፋት ወንጀል ተከሰው ፍርድ ቤት ይመላለሱ እንደነበር በወቅቱ የተዘገበ ሲሆን ጋዜጠኛ አብረሃም "የአባታችንን ስም አጥፍተሃል" በሚሉና የወያኔ የደህንነት ሰዎች ናቸው ተብለው በሚታመኑ ግለሰቦች ከፍተኛ ድብደባ እንደተፈጸመበት ይታወቃል ።

የአዲስ ነገር ጋዜጣ አዘጋጆች ለስደት ከመዳረጋቸው በፊት የወያኔ መገናኛ ብዙሃን የተለመደውን የስም ማጥፋት ዘመቻ ከፍተውባቸው እንደነበረ የሚናገሩ ምንጮቻችን፣ በሚመጣው ግንቦት ወር እንዲካሄድ ደፋ ቀና የሚባልለት ምርጫ ተብየ ድራማ ከመጀመሩ በፊት በፍርሃት ድባብ ውስጥ ሆነውም ቢሆን እንዳንድ መረጃዎችን ይፋ በማድረግ የህዝብ ልብ ሊያሸፍቱ ይችላሉ ተብለው የሚፈሩትን መኖራቸው ከቁጥር የማይገባ ነገር ግን ለወያኔ ዲሞክራሲያዊነት ዋቢ ይሆኑ ዘንድ የተተው ነጻ ጋዜጦች ከወዲሁ ለማጥፋት መወሰኑን ያመለክታል ብለዋል። ለዚህም ሽመልስ ከማል የተባለው የአገዛዙ ሎሌ በቅርቡ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ባሳተማቸው ጽሁፎች በጋዜጣው ላይ መሰረተ-ቢስ ክሶችን በማቅረብ ወያኔ ጋዜጣውን እና ሰራተኞቹን ሊተናኮል በዝግጅት ላይ እንደሆነ አመላክቶአል ይላሉ። (**ወደ ገጽ 2 ዞሯል**)

## ስድስት የወያኔ ወታደራዊ መኮንኖች መክዳታቸው ታዘገበ

የወያኔን የግፍ አገዛዝ ሲያገለግሉ የነበሩና ስድስት ወታደራዊ መኮንኖች መክዳታቸውን አጋዴን ኦን ላይን የተባለው ድህረ ገጽ ዘገበ።

ድህረ ገጹ ሰሞኑን ባወጣው ዘገባ ኮሎኔል ታደሰ፣ ካፒቴን አብርሀ፣ ካፒቴን ሀይሎ፣ ምክትል መቶ አለቃ ዳውድ፣ ም/ል መቶ አለቃ ገብሬና ም/ል መቶአለቃ ዮሀንስ የተባሉ መኮንኖች ወያኔን መክዳታቸውን ዘግቧል። ወታደራዊ መኮንኖቹ በኦጋዴን አካባቢዎች በሚደረጉት የጦር ግምባሮች እንዲሳተፉ ትእዛዝ ከተላለፈላቸው በሁዋላ መጥፋታቸውን የዘገበው ድህረ ገጹ ፣ አሁን ስለሚገኙበት ሁኔታ ግን ተጨማሪ ዝርዝር መረጃዎችን ከመስጠት ተቆጥቧል።

ለግንቦት 7 የሚደርሱት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ከሆነ አሁንም ወያኔን እየከዱ ወደ ጎረቤት አገሮች የሚጓዙ ወታደሮች ቁጥር እንደጨመረ ነው። ወታደሮቹ ለመጥፋት የሚያስችሉዋቸው ሁኔታዎች ሲመቻቹላቸው የለምንም ማመንታት እንደሚጠፉ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ ወያኔም በሁኔታው በእጅጉ እየተደናገ መጥቷል። ከቀርብ ጊዜ ወዲህ የሚከዱ የሰራዊት አባላትን ቁጥር ለመቀነስ ወያኔ የተለያዩ ጥቅማጥቅሞችን ለመስጠት ቃል መግባቱን ለማወቅ የቻልን ሲሆን፣ ሰራዊቱ ግን በወያኔ ጊዜያዊ ድለላ አለመንበርከኩን መረጃው ጠቁሟል።

## ዶ/ር ነጋሶ አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ይቅርታ መጠየቅ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ሜዳውን ለማስፋት ተጨባጭ ርምጃ መውሰድ አለበት ሲሉ ተናገሩ

የቀድሞው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ባለፈው ሳምንት አንድነት ፓርቲን በተቀላቀሉበት ወቅት ህገመንግስቱ በዲሞክራሲያዊ መንግድ ነው የጸደቀው ብለው መናገራቸው እንዳጸጸታቸው ገልጸው የኢትዮጵያን ህዝብ በይፋ ይቅርታ መጠየቃቸው የሚታወስ ሲሆን፣ በእለቱ ካስተላለፉዋቸው መልእክቶች መካከል ለዘረኛው መለስ ዜናዊ ያቀረቡት ቅድመ ሁኔታ እንደሚገኝበት ዘግይቶ የደረሰን ዜና አመልክቷል። (**ወደ ገጽ 2 ዞሯል**)

## እነ ስዩም መስፍን በቦርድ ሥም ከሚያስተዳድሩት ድርጅቶች በየአመቱ ከፍተኛ ገንዘብ እንደሚዝቁ ታወቀ

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የቦርድ ሰብሳቢ የሆነው ስዩም መስፍንና በስሩ ያሉ የቦርድ አባላት ፣አየር መንገዱ ከሚያገኘው ገቢ ውስጥ ከአንድ እስከ አምስት በመቶ የሚሆነውን እንደሚወስዱ ውስጥ አወቅ ምንጮቻች ገለጸዋል። አየር መንገዱ በእየ አመቱ ከሚያገኘው ትርፍ ውስጥ እስከ አምስት በመቶ የሚሆነውን ትርፉን ለስዩም መስፍንና በስሩ ላሉት የወያኔ ሹመኞች የሚያከፋፍል ሲሆን ለወያኔ ትልቁ የውጭ ምንዛሬ ማስገኛ ምንጭ እንደሆነም የሚታወቅ ነው።

አየር መንገዱ በዚህ አመት ከአንድ ቢለዮን ብር በላይ ማትረፉ በመገናኛ ብዙሀን መገለጹ የሚታወስ ሲሆን፣ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ለቦርድ አባላትና ለሰብሳቢው ስዩም መስፍን በመቶኛ ስሌት ድርሻ ከ50 ሚሊዮን ብር በላይ ማከፋፈሉ ታውቋል። አብዛኛው ገንዘብ ለሰብሳቢው ስዩም መስፍን የሚሰጥ ሲሆን ብዙዎች እንደሚገምቱት ከ 2001 እስከ 2002 ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ከ10 ሚሊዮን ብር ያላነሰ ገንዘብ ወደ ካዝናው ገብቷል። ስዩም መስፍን በተለያዩ ዘመዶቹ ስም በርካታ ኩባንያዎችን ከፍቶ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ በውጭ አገራት እንደሚያንቀሳቅስ የሚታወቅ ሲሆን፣ ከወያኔ ባለስልጣናት መካከል በሀብት መጠኑ ከመለስ ዜናዊና ስብሀት ነጋ ቀጥሎ በሶስተኛ ደረጃ እንደሚገኝ ምንጮቻችን ገልጸዋል።

የወያኔ ባለስልጣናት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ መሬት ለውጭ አገር ባላሀብቶች በተለይም ለቻይናውያንና ለሳኡዲ ባለሀብቶች በመቸብቸብ ላይ ሲሆኑ፣ በእያንዳንዱ የሽያጭ መሬት ውስጥ ዋናዎቹ ባለስልጣናት ከ10 በመቶ ያላነሰ ገንዘብ በጉቦ መልክ እንደሚቀበሉ ታውቋል። በርካታ የውጭ ኩባንያዎች ደህውን አርሶ አደር ከመሬቱ እያፈናቀሉ በምትኩ የራሳቸውን የግብርና ስራ በመስራት ላይ ሲሆኑ፣ ሁሉም ኩባንያዎች በየደረጃው ላሉ ባለስልጣናት የተለያየ መጠን ያለው ገንዘብ በጉቦ መልክ እንደከፈሉ " ለልዩ ልዩ ወጭዎች" ተብለው ከኩባንያዎች የሂሳብ ሰነዶች ላይ የሰፈሩ መረጃዎች እንደሚያሳዩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች ገልጸዋል።

የመሬት ችርቻሮውን የሚያካሂዱት ዋናዎች ባለስልጣኖች ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል ከሸህ ሙህመድ አላማዲን ጋር የጠበቀ ቅርበት ያላቸው ሰዎች፣ የአክሲዎን ድርሻ በመግዛት በውሰጥ ታዋቂነት የአገሪቱን መሬት በመቆጣጠር ላይ ናቸው።

## የከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኞች ውሳኔ የሚሰጡት በመለስ ዜናዊ ቀኝ በሆነው መንበረ ጸሀይ ታደሰ ቀጥተኛ ትእዛዝ መሆኑን አንድ ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ ዳኛ ጠቆሙ

በከፍተኛው ፍርድ ቤት በዳኝነት ስራ ላይ በማገልገል ላይ የሚገኙት እኒሁ ዳኛ ለግንቦት 7 ዘጋቢ በሰጡት አጭር ቃለ ምልልስ የፖለቲካ ጉዳዮችን ወይም የወያኔ ኩባንያዎችን የተመለከቱ ክሶችን በተመለከተ ውሳኔውን ጽፎ የሚያስተላልፈው ወይም ቀጥተኛ ትእዛዝ የሚሰጠው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ሰብሳቢ የሆነው መንበረ ጸሀይ ታደሰ ነው። መንበረጸሀይ የመለስ ዜናዊ የህግ አማካሪ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ የሰበር ችሎቱ ሰብሳቢና የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጠው ይሄው ሰው ነው። በመንበረ ጸሀይ ስር የተሰባሰቡት 9 ዳኞች በመላ የወያኔ ካድሬዎች መሆናቸው የሚታወቅ ሲሆን አብዱልካድር ሙህመድ የተባለው ዳኛ በተለይ ምንም የትምህርት መስፈርቱን ሳያሙዋላ ካድሬ ብቻ በመሆኑ ሹመት ያገኘ ነው።

በደረሰን መረጃ መሰረት አብዱል ካዲር ሙህመድ፣ ሂሩት መለሰ፣ታፈሰ ይርጋ፣ አልማው ወልያ፣ ሃጎስ ወልዱ፣ ብርሀኑ አመነው፣ መድህን ኪሮስ፣ በላቸው አንሺሾና ሱልጣን አባተማም የተባሉት ዳኞች የሰበር ችሎቱ አባላት ሲሆኑ፣ ዋናው ስራቸውም የወያኔን ኩባንያዎች ከሚመጡባቸው ክሶች መከላከልና የፖለቲካ ተቃውሞ የሚያነሱ ሰዎች ለሰበር ችሎት ሲያመልከቱ ወያኔን በሚጠቅም መልኩ የመጨረሻውን ውሳኔ በመስጠት ጉዳዩ እንዲዘጋ ማድረግ ናቸው። ከግንቦት 7 ጋር በመሆን መፈንቅለ መንግሥት ሊያካሂዱብኝ ስል ደረስኩባቸው ያላቸውን እነ ጄ/ል ተፈራ ማሞንና ጉዋደኞቻቸው አሁን ባለው ሁለተኛ ወንጀል ችሎት የሚፈረድባቸው ፍርድ አስቀድሞ የሚታወቅ ሲሆን፣ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ በሚያቀርቡበት ጊዜ ጉዳዮቻቸውን የሚያዩት እነዚህ ወያኔ መልምሎ ያስቀመጣቸው ዳኛ ተብየዎች እንደሚሆኑ ያገኘነው መረጃ አመልክቷል።

በሰበር ችሎት ውስጥ የተሰባሰቡት ዳኞች በሙስና የተጨማለቁ ሲሆን፣ አንዳንዶች ከ500 ብር እስከ መቶ ሺ ብር በጉቦ መልኩ እንደሚቀበሉ ለማወቅ ተችሎአል። ለእነዚህ ዳኞች ገንዘብ የሚያቀብሉት ደግሞ የወያኔ ካድሬዎች ሲሆኑ፣ በእነዚህ ዳኞችና አቀባባዮቻቸው ላይ የተለያዩ አቤቱታዎች ለአዛዣቸው መንበረ ጻሀይ ታደሰ የተነገሩ ቢሆንም፣ መንበረጻሀይ ግን አይቶ እንዳላየ ሆኖ እንደሚያልፋቸው ታውቋል። የወያኔ ኩባንያዎችና የትግራይ ተወላጆች አቤቱታ በሚያሰሙበት ጊዜ መንበረጻሀይ አፋጣኝ እርምጃ እንደሚወስድ መረጃው አመልክቷል።

## በይስሙላ ምርጫ መሳተፍ ለወያኔ አገዛዝ እውቅና መስጠት በመሆኑ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት የለውም!!!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በመሆን በአገራችን የአምባገነኖች ዑደት በወያኔ እንዲያበቃ ለማድረግ እና የማብቂያውንም ጊዜ ለማሳጠር ቆርጦ የተነሳ ድርጅት መሆኑ ዛሬ በሰፊው የታወቀ ነው ብለን እናምናለን። ከአንድ አምባገነን ወደሌላ አምባገነን ስንሸጋገር የቆየንበት ዑደት መሰበር የሚችለው በነፃና ፍትሃዊ ምርጫ የሕዝብን ይሁንታ ያገኘ መንግሥት መመሥረት ስንችል ብቻ ነው። ግንቦት7 ለእንዲህ ዓይነቱ ሰፊ ሕዝባዊ መሠረት ላለው መንግሥት ምሥረታ መንገድ አመቻች ነው።
በአገራችን የሕዝብ ፍላጎት የሚንፀባረቅበት ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ እንዲኖር ወያኔ ከሥልጣን መወገድ ይኖርበታል። የወያኔ ዓይነቱ የወንበዴዎች ድርጅት ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ አድርጎ አያውቅም። ምርጫ 97 ያረጋገጠልንም ይህንኑ ሃቅ ነው። ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ እና ወያኔ ተፃራሪዎች በመሆናቸው ሁለቱ በአንድነት ሊገኙ አይችሉም።

ከዚህ በፊትም በዚህ ጉዳይ አበክረን እንደገለጽነው ዲሞክራሲያዊ የምርጫ ሥርዓት ነፃና ፍትሃዊ እንዲሆን እና ውጤቱም ሰፊ ተቀባይነት እንዲኖረው ቢያንስ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተቋማትና ሁኔታዎች መሟላት ግድ ነው።

1. የምርጫ አስፈፃሚው አካል ከአንድ ፓርቲ ቁጥጥርና ተጽእኖ ነጻ ሆኖ የተደራጀ እና ገለልተኝነታቸው በታመነባቸው ባለሙያዎች የተገነባ መሆን ይኖርበታል፡፡
2. ፍትህን ማስፈን የሚችል የፍትህ ሥርዓት መገንባት እና በህግና በአመዛዛኝ ህሊና ብቻ ተመሥርቶ ብይን የሚሰጥበት የዳኝነት ሥርዓት መበጀት ይኖርበታል።
3. የመንግሥት የጦር ሠራዊት፣ ፖሊስ እና የሕዝብ ደህንነት ተቋማት ታማኝነታቸው ለሕዝብና ለሃገር እንጂ ለወቅቱ ጉልበተኛ አካል እንዳልሆነ ማረጋገጥ ያሻል።
4. የመንግሥት ንብረት ተቀናቃኝ ፓርቲዎችን ማዳከሚያ፣ በምርጫ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት መጠቀሚያ፣ ዜጎች የገዥው ፓርቲ አባላት እንዲሆኑ የመግዣና የማስገደጃ መሣሪያ መሆን የለበትም፡፡
5. የመንግሥት ሚዲያም ለሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶችና ለሁሉም ዜጎች መገልገያ በሚሆንበት መልኩ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ነጻና ገለልተኛ በሆነ መንገድ መደራጀት ይኖርበታል፡፡
6. በህግ የተገደበ ሥልጣን ያለው፤ ተጠያቂነት ያለበት እና የሕዝብን ውሳኔ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጀ መንግሥት ሊኖር ይገባል፡፡

የግንቦት7 ዓላማ እነዚህንና መሰል ተቋማትን በአጭር የሽግግር ወቅት በማቋቋም በነፃና ፍትሃዊ ምርጫ የሕዝብ ውክልና ያለው መንግሥት የሚመሠረትበትን ንጣፍ ማበጀት ነው። በነፃና ፍትሃዊ ምርጫ እምነት ያለው እና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል ብሎ የሚያምን ማንኛውም ድርጅት ወይም ግለሰብ ከዚህ ያነሰ አደረጃጀት ከግቡ እንደማያደርሰው ይገነዘባል ብለን እናምናለን።

እንደ ወያኔ ያለ ከተመሠረተበት እለት ጀምሮ ለሠላሳ ዓመታት ሲዋሽና ሲቀጥፍ የኖረ ወሮበላ ቀርቶ በቅን መንፈስ የተነሳሳ ለዘብተኛ አምባገነን እንኳን እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ባልተሟሉበት ሁኔታ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ማካሄድ አይችልም። ለዚህም ነው የተቋማቱ መገንባት ከምርጫው መቅደም አለበት የምንለው።

ሁሉም አምባነን ሥርዓቶች ውጤቱን የሚቆጣጠሩት ምርጫ ማድረግ ይፈልጋሉ። በአገራችንም በዘውድም በወታደራዊም የአገዛዝ ዘመናት ምርጫዎች ተደርገው ተመረጥን ያሉ ሰዎች ወጥተዋል፤ አንዳቸውም ግን የሕዝብን ስሜት የገለፁ አልነበሩም። በዚህም ምክንያት ምርጫዎቹ የገዢዎችን እድሜ አርዝመው እንደሆነ እንጂ ከአስከፊ ውድቀት አላዳኑዋቸውም። ወያኔ ከቀደሙት አምባገነኖች የበለጠ በምርጫ የመቀለድ ችሎታ ያለው መሰሪ ነው። ለራሱ ባለው የተሳሳተ ግምት ምክንያት በመጠኑ ለቀቅ ካደረገው የ97- ምርጫ በስተቀር ወያኔ ውጤቱን ሙሉ በሙሉ የማይቆጣጠረው ምርጫ ውስጥ ገብቶ አያውቅም።

ዛሬም "በስነ ምግባር ደንብ" አጃቢነት እያሳየን ያለው ዳንኪራ ከአምባገነኖች የይስሙላ ምርጫዎች እንጂ ከነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ጋር የሚያመሳስላቸው አንዳችም ነገር የለም። ወያኔ ልበ ሙሉ መስሎ ኑና "ግጠሙኝ" እያለ ያለው የምርጫው ውጤት ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ስር መሆኑን ስለሚያውቅ ነው፤ ማስተማመኛዎቹን በመዳፉ ውስጥ ጨብጧል።

- የምርጫ ቦርዱ የመለስ ዜናዊ የግል አገልጋይ ነው። ወያኔ የፈለገው እንዲያልፍ ያልፈለገው እንዲወድቅ የሚያደርጉ ካድሬዎችን ወደ ምርጫ ጣቢያዎች በመላክ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ምርጫውን ያስፈጽማል። እናም በሕዝብ ምርጫና በምርጫው ውጤት መካከል አንዳችም ትስስር አይኖርም፡፡
- ከምርጫው በፊትም ሆነ በኋላ- የወያኔ ራድዮ፣ ቴሌቪዥንና ፕሬስ ስለ ወያኔ ሆደሰፊነትና ስለ ምርጫው እንከን የለሽነት ይሰብኩናል፤ ለማስረጃም ከአጃቢዎችም አንዳንድ ስሞች አሸናፊዎች ዝርዝር ውስጥ ጣል ጣል መደረጋቸው አይቀርም።
- ድንገት ያልተጠበቅ ነገር ካጋጠመም ህግ ያልገደበው ሥልጣን ያለው ወያኔ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጆም ሆነ ሳያውጅ ግንባርና ልብ ላይ የሚተኩሱ ወታደሮቹን በሰላማዊ ሕዝብ ላይ ለማዝመት ዘወትር ዝግጁ ነው።
- ምናልባት ውጤት ነው የተባሉትን ለመቀበል የሚያንገራግሩ ከተገኙ የወያኔን ውሳኔ በህግ አንቀጾች አሽሞንሙነው በሚያነቡ ሃሳዊ ዳኞች የሞት ወይም የእድሜ ልክ እስራት ይበየንባቸዋል።

አገራችን ያለችበት መራር ሃቅ ይህ ነው። ሰሞኑን እየተወራለት ያለው የስነምግባር ደንብን ያመጣው አንዳችም አዲስ ነገር የለም። ጥሩ ይሁን መጥፎ፤ ሙሉም ይሁን ጎደሎ ስነምግባሩን የሚያስፈፅም ከወያኔ ነፃ የሆነ አንድም አካል የለም። ስለሆነም ስምምነቱ ተፈፃሚ የሚሆነው ወያኔን እስከጠቀመ ድረስ ብቻ ነው። በአሁኑ ሰዓት ይህንን የሚጠራጠር ኢትዮጵያዊ ይኖራል ብሎ መገመት ያስቸግራል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በምርጫ ፓለቲካ የደረሰበት የብስለት ደረጃ የውጭ ዜጎች ብቻ ሳይሆን በምርጫ ስለመሳተፍ ጠቃሚነት የሚሰብኩን የኛዎቹ ፓለቲከኞችም ከሚገምቱት በላይ ነው። በዚህም ምክንያት ለወያኔም ሆነ ለእነሱ- ውትወታ ሕዝቡ ጆሮ እንደማይሰጥ ጥርጣሬ የለንም። ኢትዮጵያን ከወያኔ መዳፍ ነፃ ለማውጣት እንታገላለን የሚሉ የፓለቲካ ድርጅቶችና ግለሰቦች "እውነት የሕዝቡን የብስለት ደረጃ የሚመጥን የትግል ስልት መርጫለሁን? ይህን ትግል ለመምራትስ ዝግጁ ነኝን?" ብለው እንዲጠይቁ እንመክራለን::

በተረፈ ከሚቀጥለው ምርጫ የምንጠብቀው አንዳችም በጎ ነገር የለም። ምርጫው የሕዝብን ፍላጎት የሚገለጽበት ትንሽም እንኳን እድል ፈጽሞ የለም። በይስሙላ ምርጫ መሳተፍ ለወያኔ አገዛዝ እውቅና መስጠት በመሆኑ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት የለውም!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## የአዲስ ነገር ጋዜጣ አዘጋጆች ከወያኔ ... ከገጽ 1 የዞረ

ይህ በእንዲህ እንዳለ በወያኔ የሃይል ቁጥጥር ስር የሚገኘው የኢትዮጵያ ቴሌቪዢን አገልግሎት፣ የአዲስ ነገር ጋዜጣን እና ሰራተኞች ክፉኛ የሚወነጅል ፕሮግራም አዘጋጅቶ አየር ላይ ለማቅረብ በዝግጅት ላይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።
የጋዜጣው አዘጋጆች እና ጋዜጠኞች ሞያቸው በሚጠይቀው መልኩ ነፃ ሆነው ለመፃፍ የሚያስችላቸው ምህዳር በኢትዮጵያ ውስጥ እንደሌለ ቀድሞውኑ አውቀው የገቡበት ቢሆንም፤ እየገፋ ያለው ጫና እና የሰሞኑ የወያኔ ማስፈራራት ግን ባለው ሁኔታ መቀጠል እንደማይችሉ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ እንዳደረጋቸው ለጋዜጣው ቅርብ የሆኑ ምንጮቻችን ገልጸዋል። የወያኔ አሰራር ያልጠፋቸው የጋዜጣው አዘጋጆችም የቴሌቪዢን አገልግሎቱ ያዘጋጀውን በውንጀላ የተሞላ ዝግጅት እንደ መጨረሻው ምልክት በማየት ጋዜጣውን ዘግተው አገር ጥለው ለመውጣት ተገደዋል።
አለም አቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተከራካሪ ድርጅት ሲፒጄ በየጊዜው በሚያወጣው ሪፖርቱ ኢትዮጵያ የሃሳብን ነጻነት ከሚገድቡ ፍጹም አምባገነን አገሮች አንዷ መሆኗን በመግለጽ በጋዜጠኞች ላይ የሚፈጸመው ማስፈራራት፣ እስርና ስደት በአስቸኳይ እንዲቆም በተደጋጋሚ ጠይቆአል። የአለም አገራትን የፕሬስ → ነፃነት ደረጃ ለማሳየት በአለም አቀፍ ደረጃ የሚወጡ የተለያዩ ሪፖርቶችም አገራችን ከበስተመጨረሻዎቹ መጥፎ አገሮች ተርታ መሆኗን እንደሚያሳይ ይታወቃል። አገር ጥለው በሚሰደዱ እና በሚታሰሩ ጋዜጠኞች ቁጥርም አገራችን ከመላው አለም ከፍተኛውን ደረጃ ይዛ ትገኛለች።

## ዶ/ር ነጋሶ አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ይቅርታ ... ከገጽ 1 የዞረ

ዶ/ር ነጋሶ ሲናገሩ "የፖለቲካ ምህዳሩ ለሁሉም እና ህጋዊ ፓርቲዎች እኩል እና ፍትሀዊ መሆኑን ለማረጋገጥ እርስዎ የሚመሩት የፖለቲካ ድርጅት በህገወጥ መንገድ በህዝብ ንብረትና ገንዘብ እና የሰው ሀይል ስትጠቀሙ እንደነበር በይፋ ይመኑ፤ ወ/ት ብርቱካንና ሌሎች የፖለቲካ እስረኞች የምርጫው ሂደት ከመጀመሩ በፊት እንዲፈቱ ሁኔታውን ያመቻቹ፣ ሀሉም ህጋዊና ሰላማዊ የፖለቲካ ድርጅቶች ከዚህ ሳምንት ጀምሮ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች በመንቀሳቀስ የድርጅት ስራዎቻቸውን እንዲያከናውኑ ለዚህም ቢሮዎቻቸውን ባስቸኳይ ለመክፈት እንዲችሉ ምንም አይነት እክል እንዳይገጥማቸው መመሪያዎችን በብዙሀን መገናኛ ያስተላልፉ፣ የመንግስት መገናኛ ብዙሀን ያለ አድልዎ ሁሉንም ፓርቲዎች እንዲያገለግሉ ትእዛዝ ያስተላልፉ። በህገመንግስቱ የተደነገጉ ሰብአዊ መብቶችና ነጻነቶች የሚጻረሩ ህጎች እንዲቀየሩ ወይንም እንዲሻሻሉ ሁኔታዎችን **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

**በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን**

**የፖስታሳጥን ቁጥር :-** POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ሃይለ ሀሳብ

## የዘረኞች ፍርድ ነፃነታችንን አያዘገየዉም!

በተፃፈ ህግና በራሱ ህሊና ሳይሆን በዘረኞች ትዕዛዝ የሚመራዉ የወያኔ አቃቤ ህግ ባለፈዉ ማክሰኞ መለስ ዜናዊ "የግንቦት ሰባት ተከሳሾች" እያለ የሚጠራቸዉን ሰዎች በሞት ቅጣልኝ ብሎ የላከለትን ደብዳቤ ለይስሙላዉ ፍረድ ቤት በንባብ በማሰማት በእርግጥም ኢትዮጵያ ፍትህ አልባ አገር እንደሆነች እንደገና በተግባር አረጋግጧል። ይህ መረን የለቀቀ የቂም በቀል አሰራር ፍርድ ቤቶችን እንደግል ተቋሙ የሚጠቀምባቸዉ መለስ ዜናዊ በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ የኢትዮጵያ ህዝብ መብትና ነፃነት እንደማይከበር በይፋ አሳይቷል። ከታሪክ መማር በጭራሽ የማይሆንላቸዉ አምባገነኖች የነፃነትን እሳት ማጥፋት የሚችሉ እየመሰላቸዉ የሚወስዱት ፀረ-ህዝብ እርምጃ ጭራሽ እሳቱን እያቀጣጠለ አነሱኑ አቃጥሎ ሲፈጃቸዉ በየዘመኑ ታይቷል። ከትናንትናዎቹ የደርግ አምባገነኖች አይወድቁ አወዳደቅ ትምህርት መቅሰም የተሳነዉ መለስ ዜናዊ ለህዝብ መብትና ነፃነት የቆሙ ጀግኖችን በሞት ስለቀጣ ብቻ ተረጋግቶ የሚኖር መስሎት ይሆናል። ነገር ግን - ነገሩ "በቅሎ መታሰሪያዋን በጠሰች በራሷ አሳጠረች" ነዉና የጀግኖች ሞት ጀግኖችን እያፈራ የወያኔን ስርዐት ግብአተ መሬት ያፋጥናል እንጂ መለስ ዜናዊ ያሻዉን ቢያደርግ የህዝብን የነፃነት ፍላጎት ማፈን አይችልም።

የመለስ ዜናዊ ታማኝ አገልጋይ የሆነዉ የፌዴራል አቃቤ ህግ ሰሞኑን ከጌታዉ የተላከዉን የቅጣት ማክበጃ ደብዳቤ ለፍርድ ቤቱ በንባብ ሲያሰማ እንደዚህ ነበር ያለዉ፡ "አጥፊዎቹ ሌላ ወንጀል እንዳይፈጽሙ ለመግታት ለመሰሎቻቸዉ ቅድመ ማስጠንቀቂያና መቀጣጫ ለተቀረዉ ደግሞ ማስተማሪያ እንዲሆን የተቀመጠዉ ቅጣት ጣሪያ የሆነዉ የሞት ቅጣት እንዲወሰንባቸዉ እጠይቃለሁ"።

አዎ! መለስ ዜናዊ የነፃነታችን ሁሉ የበላይ የሆነዉን ለመብትና ለነፃት የመታገል ነፃነታችንን እንደ ወንጀል ቆጥሮታል። ዘረኛዉ መለስ ዜናዊ - ህዝብ አይረገጥ፤ ነፃነት ይከበር፤ ዘረኝነት ይጥፋ የስልጣን ብቸኛ ምንጭ ህዝብ ነዉ የሚለዉን የኢትዮጵያ ህዝብ ጩኸት እንደተራ ረብሻና አመጽ ቆጥሮታል። በአጠቃላይ እሱ ብቻ ሳይሆን ሂሊና ቢሶቹ የወያኔ ሹማምንት ህዝብን ያስፈራሩ መስሏቸዉ ጥቂት የነፃነት ተሚጋቾችን አስረዉ በሞት እንቀጣለን ብለዋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ግን መለስ ዜናዊ፤ ዘረኛ ፓርቲዉ ህወሀትና አንዳንድ ሂሊናቸዉን ሸጠዉ ለሆዳቸዉ ብቻ ያደሩ ሹምባሾች በግልፅ እንዲረዱት የሚፈልገዉ አንድ እዉነት አለ። እነሱ ወደዱም ጠሉም የኢትዮጵያ ህዝብ መብትና ነፃነት እስካልተከበረና ዘረኝነት ከኢትዮጵያ ምድር እስካልጠፋ ድረስ የተጀመረዉን ህዝባዊ ትግል ማቆም የሚችል ምንም ምድራዊ ኃይል የለም። መለስ ዜናዊ እንዳሰኘዉ ቢያስርና ቢገድል ትግሉን የበለጠ ያጠናክረዋል እንጂ ህዝብን ማስፈራራት አይችልም። የኢትዮጵያ ህዝብ ለሱ መብትና ነፃነት መከበር ሲታገሉ መስዋዕት ከሚሆኑ ልጆቹ ጀግንነትን፤ ጽናትንና ቆራጥነትን እንጂ ፍርሀትንና ተስፋ መቁረጥን ተምሮ አያዉቅም። ከዛሬ በኋላ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚፈራዉ ለነፃት መሞትን ሳይሆን ያለ ነፃነት መኖርን ነዉ። የኢትዮጵያን ወጣት ያንገሸገሸዉና እልህ ዉስጥ የከተተዉ ለነፃነቱ ሲታገል ታስሮ ቃሊቲ መግባቱ ሳይሆን ዕድሜ ልኩን ተምሮ ለስራ ሲደርስ ስራ ለማግኘት ማንነትህን ለዉጥ መባሉ ነዉ። ሠራተኛዉንና ወታደሩን ቀንና ማታ እረፍት የሚነሳቸዉ ነገ የሚጠብቃቸዉ ህይወት የሚያስከፈል ትግል ሳይሆን ከሰዉ በታች ያደረጋቸዉ የወያኔ የዘረኝነት ፓሊሲ ነዉ። ዛሬ ለግዜዉም ቢሆን መለስ ዜናዊ 'ቀን የወጣለት ቂል' ነዉና ጥቂት ጀግኖችን ማሰርና መግደል ይችል ይሆናል። ሆኖም ማድርግ የሚችለዉን ነገር ሁሉ ቢያደርግ በዉስጣችን የሚቀጣጠለዉን የነፃነት መንፈስ ማሰርም ሆነ መግደል አይችልምና በቀቢፀ-ተስፋ የሚወስዳቸዉ እርምጃዎች መንፈሳችንን ያነቃቁታል እንጂ አያስጨንቁንም!

አንድን ሰዉ በሞት የሚያስቀጣዉ ወንጀል ለመፈጸም ማቀዱ ሳይሆን ያሰበዉን ወንጀል ፈጽሞ ሲገኝ ነዉ። በጄኔራል ተፈራ ማሞ ሰነድ የተከሰሱት ተከሳሾች ለህዝብ ነፃነት ታገሉ እንጂ ወንጀል አልፈጸሙም። ይህ እነ ጄኔራል ተፈራ ዘረኝነትን ከኢትዮጵያ ምድር ለማጥፋት የቀየሱት ቅዱስ እቅድ በወያኔ ፍርደ-ገምድሎች ወንጀል ነዉ ተብሎ ቢቆጠር እንኳን የተመሠረተባቸዉ ክስ "አቀዱ" እንጂ "ፈጸሙ" ስለማይል ተከሳሾቹን ለሞት የሚያበቃ ምንም ነገር የለም። ሆኖም የመለስ ዜናዊ የፖለቲካ መሳሪያ የሆነዉ ፍርድ ቤት ህጉ የሚጠቅሰዉን ሳይሆን ከቤተ መንግስት በስልክ የተነገረዉን ፈርድ ለመፍረድ በዝግጅት ላይ ይገኛል። የወያኔ የህግና ፍትህ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ተብዬዉ መኮንን ቤዛነህ በአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ዘጋቢ ተጠይቆ ሲመልስ እንዲህ ነበር ያለዉ - "ተከሳሾቹ የሞት ፍርድ እንዲፈረድባቸዉ የጠየቅነዉ ጥፋታቸዉን ቆጥረንና ደምረን ነዉ፤ በእኛ ህግ መሠረት አንድ ሰዉ በብዙ ጥፋቶች ከተከሰሰ ጥፋቶቹ ተቆጥረዉ ድምሩ የሞት ፍርድ ሊያስፈርድ ይችላል" ብሏል። እንግዲህ ኢትዮጵያ ዉስጥ አንድ ሰዉ ወንጀል ለመፈፀም ካሰበ፤ ከተናገረና ካቀደ ያቀደዉን ቢፈፅምም ባይፈፅምም ማሰቡ፤ መናገሩና ማቀዱ ተደምረዉ ለሞት ፍርድ ያበቁታል ማለት ነዉ።

የመለስ ዜናዊ ፍርድ ቤት አንደኛዉ ገፅታ አስቂኝ የድራማ ቦታ መሆኑ ነዉ። የሚገርመዉ ብዙ ሰዉ ወደ ወያኔ ፍርድ ቤት የሚሄደዉ ፍርድ ሲፈረድ ለማየት ሳይሆን አቃቤህጉና እሱ ያሰለጠናቸዉ ምስክሮች የሚያሳዩት ድራማ እየናፈቀዉ ነዉ። ባለፈዉ ማክሰኞ ፍርድ ቤቱ ዉስጥ የተገኘዉን ታዛቢ እንደ ህፃን ልጅ በሳቅ ካንከተከተዉ ነገር አንዱ ኮሜዲያኑ አቃቤ ህግ በሪሁ ተወልደብርሐን ለፍርድ ቤቱ ያስደመጠዉ ንግግር ነበር። ይህ የተፃፈ ህግን ሳይሆን መለስ ዜናዊ የላከለትን ማስታወሻ እየጠቀሰ የተናገረዉ ሂሊና ቢስ ግለሰብ እንዲህ ነበር ያለዉ:-

> *"ተከሳሶቹ የፈፀሙት ወንጀል ፍፃሜ አግኝቶ ቢሆን ኖሮ የአገሪቱን አንድነት የሚበታትን በአገር ህልዉና ላይ ያነጣጠረ የአንድን ወገን ፍላጎት በሌሎች በሔረሰቦች ላይ የሚጭን አደገኛ አድራጎት ነበር"።*

የአቃቤ ህግ ተቀዳሚ ተግባር መንግስትን ጨምሮ የህዝብን መብት የሚደፍሩ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን ተከታትሎ ለፍርድ ማቅረብና በዳይም ሆነ ተበዳይ ትክክለኛ ፍርድ እንዲያገኙ ማድርግ ነዉ። በሪሁ ተወልደበርሐን ይህንን ተቀዳሚ ተግባሩን በትክክል የሚያዉቅ ቢሆን ኖሮ የኢትዮጵያን አንድነት በተመለከተ ለፍረድ ማቅረብ የነበረበት ለአገር አንድነት የተዋደቁትን ጀኔራል ተፈራንና ጀኔራል አሳምነዉን ሳይሆን አገር እየቆረሰ ለጎረቤት የሚያድለዉን መለስ ዜናዊን ነበር። ዛሬ ኢትዮጵያ ዉሰጥ እጅና እግሩን ታስሮ ቃሊቲ መወርወር የነበረበት "አገሬን ከሚመጣዉ አደጋ ለማዳን እርምጃ መዉሰድ ነበረብኝ" ያለዉ ጀግናዉ ብርጋዴር ጀኔራል ተፈራ ማሞ ሳይሆን- በዘር ማጥፋት ወንጀል የሚፈለገዉ ዘረኛዉ መለስ ዜናዊ ነበር።

ከመለስ ዜናዊ በፊት በነበሩት መንግስታት ወቅት ኢትዮጵያ ዉስጥ የብሔረሰቦች መብት፤እኩልነትና ነፃነት የተከበረ ነበር የሚል አስተያየት በፍፁም የለንም። ሆኖም አንድ ብሔረሰብ በሁሉም ዘርፍ ሌሎችን ረግጦ የገዛበት እንደ ወያኔ አይነት አገዛዝ አገራችን ኢትዮጵያ አይታ አታዉቅም። ሥራ ለማግኘት፤ አለቃ ለመሆን፤ ጨረታ ለማሸነፍ፤ የነፃ ትምህርት ዕድል ለማግኘት፤ ቁልፍ በሆኑ ዘርፎች የንግድ ፈቃድ ለማግኘትና በአጠቃላይ ሰዉ ሆኖ ለመኖር- ኢትዮጵያዉያን ወይ መለስ ዜናዊ "ወርቃማዉ ዘር" እያለ ከሚጠራዉ ዘር መወለድ አለባቸዉ፤ አለዚያም ሂሊናቸዉን ሽጠዉና "ወይን ለመኖርን" ተከትለዉ የወያኔ ታማኝ አገልጋይ መሆን አለባቸዉ። እዚህ ላይ አድማጭ ልብ ሊለዉ የሚገባ አንድ ነገር አለ። የመጀመሪያዉ ምርጫ ማለትም ከወርቃማዉ ዘር መወለድ በተፈጥሮ የሚገኝ እንጂ ማንም መምረጥ የሚችለዉ ምርጫ አይደለም! እንገዲህ ወያኔ በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ ኢትዮጵያዉያን ያለን ምርጫ ተገዝተን መኖር ወይም ለነፃነትና ለእኩልነት መታገል ነዉ።

መለስና ጓደኞቹ ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ አለ የሚሉን የብሔረሰቦች እኩልነት አንድን ብሔረሰብ ገዢና የበላይ ሌሎችን ደግሞ በጥቅሉ ተገዢና የበታች የሚያደርገዉን የወያኔ የዘረኝነት ፖሊሲ ነዉ። እንግዲህ ወያኔዎች እኩልነት የሚሉት እነሱ "ወርቃማዎቹ" የበላይ ሆነዉ ሌላዉ ሁሉ የበታች ሆኖ አሜን ብሎ ሲገዛላቸዉ ነዉ። ይህንን መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያ ዉስጥ በኃይል የፈጠረዉን አስቀያሚ የገዢነትና የተገዢነት ስርአት እንኳን አዋቂዉ አቅመ አዳም ያልደረሰ ህፃን ልጅም በሚገባ የሚያዉቀዉ ጉዳይ ነዉ። ዛሬ ቁልጭ ባለ መልኩ የወያኔ የኤኮኖሚና የፖለቲካ ፍላጎት በሌሎች የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ላይ እንደቀንበር ተጭኖ እየታየ የዚህ ወገናዊ ስርአት ተቆርቋሪ የሆነዉ አቃቤህግ በሪሁ ተወልደብርሀን ፍርድ ቤት ዉስጥ ያደረገዉ የድፍረት ንግግር የሚገርም ባይሆንም ብዙዎቻችንን እልህ ዉስጥ እንደከተተ የሚዘነጋ አይደለም። እንግዲህ ይታያችሁ ጀኔራል ተፈራ ማሞ ለስርአቱ ቁንጮዎች ደግመዉ ደጋግመዉ የሰጡት ማስጠንቀቂያ - "የኢትዮጵያ ጦር በትግራይ ተወላጆች ቁጥጥር ስር ወድቋል፤ በሠራዊቱ ዉስጥ የሌሎች ብሔረሰብ አባላት እንደ ሁለተኛ ዜጋ ይቆጠራሉ፤ እንደዚህ አይነት አሠራር ለአገራችን አንድነት አይጠቅምምና መቆም አለበት" የሚል አገር አድን ማስጠንቀቂያ ነበር። እኚህን የመሰሉ ለአገርና ለወገን ተቆርቋሪ ጀኔራል ነዉ በሪሁ ተወልደብርሀን የአገርን አንድነትና የብሐረሰቦችን እኩልነት ሊያፈርሱ ነዉ ብሎ የሞት ፍርድ እንዲሰጣቸዉ የጠየቀዉ!

ሠላምና ነፃነት ፈላጊዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ! ወያኔ ላንተ መብት፤ ነፃነትና ብልፅግና የሚታገሉትን ልጆችህን እያደነ የሞት ፍርድ የሚፈርድባቸዉ አንተን ለማስፈራራትና አንገትህን ደፍተህ እንድትገዛ ለማደርግ ነዉ። በተለይ የወደፊቷን ኢትዮጵያ ተረካቢ የሆነዉ ወጣቱ ትዉልድ ለወያኔ ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛ ብዙ ፈተናዎች እየተደረደሩበት ነዉ። ዘረኛዉ መለስ ዜናዊ ፊት ለፊት ተጋፍጦ የሚያንበረክከዉና ዘረኝነትን ከኢትዮጵያ ምድር የሚያጠፋዉ ወጣቱ እንደሆነ በሚገባ ያዉቃል፤ ለዚህ ነዉ የሚቃወመዉን ወጣት በአደባባይ እየገደለ የሚታገለዉን እያሰረ የቀረዉን ደግሞ ከወየናችሁ ስራ እሰጣችኋለሁ እያለ የወጣቱን ትዉልድ የነፃነትና የአትንኩኝ ባይነት መንፈስ ለመስበር የሚታገለዉ። ቆራጡ የኢትዮጵያ ወጣት ግን የዘረኞችን ወጥመድ በጣጥሶ ለመብትና ለነፃነት የሚደረገዉን ትግል በግንባር ቀደምትነት እንደሚቀላቀል ሙሉ እምነታቸን ነዉ።

የኢትዮጵያ ወጣት ወያኔን በማስወገዱ ትግል ዉስጥ ግንባር ቀደሙን ሚና መጫወት አለበት የምንለዉ ወጣቱ የወደፊቷን ኢትዮጵያ ተረካቢ ስለሆነ ብቻ አይደለም። የወጣቱ ትወልድ የነፃነት ጥማትና ይህንን ትግል ተሸክሞ ከግብ የማድረስ ችሎታ ከዬትኛዉም የህብረተሰብ ክፍል የበለጠና የተሻለ ስለሆነም ጭምር ነዉ። አማራጭ አጥተህ ወያኔን በዉትድርና የምታገለግለዉ ኢትዮጵያዊ ወጣት ሆይ - ወያኔ አንዴ ወገኖችህ ላይ እያስተኮስ ሌላ ግዜ ደግሞ ለአገርህ በማይጠቅሙ ጦርነቶች ላይ እያዘመተህ በጥፋት ላይ ጥፋጥ የምትሰራ ኃይል አድረጎሀል። ከዛሬ በኋላ ግን የወያኔ አዛዦች የሚሰጡህን ትዕዛዝ አጥብቀህ መመርመር ይኖርብሀል፤ አንዳንዴ ተዋግተህ ብታሸንፍ እንኳን የተገኘዉ ድል የኢትዮጵያን ጥቅም የሚጎዳ ከሆነ በእንደዚህ አይነቱ ጦርነት ላይ አትሳተፍ፤ በተለይ በራስህ ወገን ላይ ጥቃት ፈፅም የሚልን የወያኔ ትዕዛዝ በፍፁም አትቀበል። ዛሬ ላንተና ወገንህ ለሆነዉ የኢትዮጵያ ህዝብ መብትና ነፃነት መከበር አምርረዉ የተነሱ ወንድሞችህና እህቶችህ አሉ፡ አመቺ ሁኔታ ባገኘህ ግዜ ሁሉ የእነዚህን ወገኖች ጥሪ ተቀብለህ የታጠከዉን የህዝብ መሳሪያ በዘረኞችና በፀረ-ህዝቦች ላይ አንሳ!

በዬትኛዉም ክልል ተወልዶ የሚያድግ ኢትዮጵያዊ የወደፊት ዕድል የሚወሰነዉ በሚናገረዉ ቋንቋና በተወለደበት ጎሳ ሳይሆን በችሎታዉና በባህሪዩ እስኪሆን ድረስ የኢትዮጵያ ህዝብ የነፃነትና የእኩለነት ትግል ይቀጥላል። ይዋል ይደር እንጂ ይህ ትግል በኢትዮጵያ ህዝብ አሸናፊነት ይገባደዳል። በዚህ ምሽት ይህንን መልዕክት ለምታዳምጥ ዜጋ ሁሉ ትልቁ ጥያቄ በዚህ የሞት የሽረት ትግል ዉስጥ ያንተ ወይም ያንቺ ድርሻ ምንድነዉ የሚለዉ ጥያቄ ነዉ። ነፃነትን የመሰለ ነገር ተቀምተሽ እየሰገድሽ በባርነት ትኖሪያለሽ ወይስ ታግለሽ ነፃነትሽን ታስከብሪያለሽ? አንተስ ነፃነትን የመሰለ ክቡር ዕቃ ለዘረኞች አስረክበህ አንተና ልጆችህን ተገዢ ታደርጋለህ ወይስ የተቀማኸዉን ነፃነት በትግል ታስመልሳለህ? የትዉልድ አደራ አለብኝ ወይም ነፃነት ወይም ሞት የምትል ኢትዮጵያዊ ሁሉ የግንቦት ሰባትን የነፃነትና የአገር አድን ጥሪ ተቀብለህ አንተንና ቤተሰብህን ከግዞትና ከዉረድት አገርህን ደገሞ ከመበታተን አድን!

## በርካታ ህዝብ በተጨማሪ እሴት ታክስ ክፉኛ መማረሩን ሪፖርተራችን ከአዲስ አበባ ዘገበ

የግንቦት 7 ዘጋቢ ባስተላለፈው ዘገባ በተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም ቫት እየተባለ በሚጠራው ግብር በርካታ ህዝብ በእጅጉ በመማረርና ላለመክፈልም ተቃውሞውን በማሰማት ላይ ነው።

ቫት ገቢያቸው ከ500 ሺ ብር በላይ የሆኑ ነጋዴዎችን ልዩ ግብር ለማስከፈል ተብሎ የተቋቋመ ሲሆን ፣ በአሁኑ ጊዜ ግን ጉልት ነጋዴዎች ሳይቀሩ ቫት እንዲከፍሉ እየተገደዱ መሆኑን ሪፖርተራችን አክሎ ገልጾአል። ህዝቡ በኑሮ ውድነቱ የጠነሳ በየሻሂ ቤቶች ገብቶ ለመጠቀም አለማቻሉን የገለጹት ደግሞ የሆቴል ባለቤቶች ሲሆኑ፣ ወያኔ የህዝቡን መጎሳቆል ሳይመለከት የሚጥለው ታክስ ብዙዎች ድርጅቶቻቸውን እንዲዘጉ እያስገደዳቸው ነው። ሻሂ በትንንሽ ሻሂ ቤቶች ከ1.50-2.00 ብር፣ ቡና ደግሞ ከ3.00 - 4.00 ብር እንደሚሸጡ የገለጸው ዘጋቢያችን ባለሻሂ ቤቶች የቫት እዳቸውን ለመክፈል ዋጋዎችን ሲያንሩ ፣ ህዝቡ ደግሞ ለመክፈል በመጀገሩ ወደ ሻሂ ቤቶች አዘወትሮ አይሄድም። የዋጋዎች ማነርና የህዝቡ የመክፈል አቅም አለመመጣጠን የተለያዩ አነስተኛ ድርጅቶች እንዲዘጉ እያደረገ መሆኑን ዘገባው አመልክቷል።

ግብር መክፈል የወያኔን እድሜ ማራዘም፣ የወያኔን እድሜ ማራዘም ደግሞ ስቃይን ማራዘም በመሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ በተቻለው አቅም ሁሉ ግብር እንዳይከፍል ግንቦት 7 ሲያሳስብ መቆየቱ የሚታወስ ነው።

## በድህረ ምርጫ 97 በተዘጉት ጋዜጦች ባለቤቶች ላይ ወያኔ የሚወስደው የበቀል እርምጃ አሁንም አልቆመም

ወያኔ ከምርጫ 1997 በፊት ሲታተሙ የነበሩ ጋዜጦችን ካፈነና አሳታሚዎችንና ዋና አዘጋጆችን አስሮ ሲያሰቃይ ከቆየ በሁዋላ ፣ አሁን ደግሞ የበቀል በትሩን እንደገና መምዘዙ ታውቋል። የአስኳል፣ ሚኒሊክና ሳተናው አዘጋጅ የነበረው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ እንደዘገበው የወያኔው ፍርድ ቤት አሳታሚዎቹ የፊታችን አርብ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ትእዛዝ ማስተላለፉን ዘግቧል። የኢትዮጵ እና የአባይ ጋዜጦች ባለቤት የነበረው ሲሳይ አጌና፣ የ ነጻነት አሳታሚ የነበረው ዘካሪያስ ተስፋየ፣ የአስኳል፣ የሚኒልክና የሳተናው ጋዜጦች አሳታሚ ሰርካለም ፋሲልና በአሁኑ ሰዓት በስደት ላይ የሚገኘው የቀድሞው የአዲስ ዜና አሳታሚ ፋሲል የኔአለም ጠቅላይ ፍርድቤት እንዲቀርቡ ታዘዋል። የወያኔው ከፍተኛ ፍርድ ቤት አሳታሚዎቹ በአገሪቱ ፕሬዚዳንት ግርማ ወልደጊዮርጊስ ምህረት የተደረገላቸው በመሆኑ እንዲከፍሉ የተጠየቁትን ገንዘብ መክፈል እንደማይገባቸው ትእዛዝ አስተላልፎ የነበረ ቢሆንም፣ ወያኔ ግን ምህረቱ የጋዜጦች ባለቤቶችን አይመለከትም ሲል ተናግሯል።

በጋዜጣ አሳታሚዎች ላይ ተጥሎ የነበረው ቅጣት በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ሲሆን፣ ወያኔ የአሳታሚዎቹ ንብረት የሆኑ ነገሮች በሙሉ እንዲያዙ ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ጥያቄ አቅርቧል። ወያኔ በዚህ ሰአት የተዘጉ ጋዜጦች ባለቤቶችን ለማሳደድ የፈለገው ምርጫው እየተቃረበ በመምጣቱ ሊሆን እንደሚችል ጋዜጠኛ እስክንድ አስተያየቱን ያሰፈረ ሲሆን፣ ሌሎች ወገኖች እንደሚሉት ግን እርምጃው ከወያኔ የተለመደ የበቀል ባህሪ ጋር አብሮ መታየት ይኖርበታል። ወያኔ በአሁኑ ጊዜ በአገር ውስጥ ያሉ ጋዜጦችንና የፖለቲካ ፓርቲዎችን በሙሉ ያዳከመ በመሆኑ በመጪዎ ምርጫ የሚሰጋበት ነገር የለም የሚሉት አስተያየት ሰጪዎች፣ በቀድሞ የጋዜጣ ባለቤቶች ላይ የጀመረው ማሳደድ ወያኔ ግለሰቦችን ለመበቀል ካለው ፍልጎት የመነጨ ነው።

በግንቦት 97 ምርጫ ወቅት የታገዱት ጋዜጦች የነበራቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደነበር የሚታወስ ሲሆን፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጠንካራ የሚባሉትን ጋዜጦች ለማጥፋት ወያኔ ሌት ተቀን ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። በርካታ ጋዜጠኞች የደረሰባቸውን ጫና መቋቋም ባለመቻላቸው ወይም ወያኔን በውጭ አገር ሆነው ለመፋለም በመወሰናቸው አገር ጥለው መጥፋታቸው የሚታወቅ ሲሆን፣ ከቀድሞ ጠንካራ ጋዜጦች አሳታሚዎች መካከል በአገር ውስጥ የቀሩት ሶስቱ ብቻ ናቸው። እነዚህ አሳታሚዎች ፈቃድ ለማግኘት በተደጋጋሚ ጥያቄ አቅርበው በወያኔ ባለስልጣናት መከልከላቸው የሚታወስ ሲሆን፣ አሳታሚዎቹ ከእስር ከተፈቱበት ጊዜ ጀምሮ ያለምንም ስራ በመቀመጣቸው በራሳቸውና በቤተሰቦቻቸው ላይ ከፍተኛ የሆነ የአእምሮ ጉዳት እየደረሰባቸው እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል።

ወያኔ የህዝብን የማወቅ ና መረጃ የማግኘት መብቶች በማፈን በስልጣን ላይ ለረጂም ጊዜ እቆያለሁ ብሎ እንደሚያልም ተደጋግሞ የተዘገበ ሲሆን ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ይህ ህልሙ እየተነነ በመምጣት ላይ መሆኑን ብዙዎች ይናገራሉ። ህዝቡ ግንቦት 7ትን ለመሳሰሉት የመገናኛ ብዙሀን ከፍተኛ ትኩረት እየሰጠ በመምጣቱ ከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ የገባው ወያኔ፣ ከቻይና ባስገባው ቴክኖሎጂ የሬዲዮ አፈና ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ መሆኑም መዘገቡ ይታወሳል። በቅርቡ ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለከተው ወያኔ የግንቦት 7ትን ራዲዮ ለማፈን በርካታ ዶላሮችን የሚያፈስ ሲሆን፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በገጠመው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እጥረት አፈናውን በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ ለማድረግ ተገዷል።

## የመለሰ ዜናዊን ፋሽስታዊ አገዛዝ የሚቃወም ሁለት ታለላቅ ሰላማዊ ሰልፎች በሚቀጥሉት ሳምንታት ውስጥ ሊደረጉ ነው

መለስ ዜናዊ በአገራችንንና በወገኖቻችን ላይ የሚፈጽማቸውን ፋሽስታዊ አገዛዝ ለማውገዝና ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ጆሮ ዳባ ልበስ ያሉትን ምዕራባዊያን አገሮችን ትኩረት ለመሳብ በአውሮጳ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በፈረንጆች አቆጣጠር ዲሰምበር 9 2009 በጄነቫ ሲዊዘር ላንድ የአምባገነኑ መለስ ዜነዊ የሰብአዊ መብት አያያዝ በአለም መንግስት ፊት በሚገመገምበት ወቅት ከተባበሩት መንግሥታት ጽ/ቤት ፊት ለፊት ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ የሚጀምር ነው። የሰልፉ አስተባባሪዎች ባወጡት መግለጫ ፣ “የመለስ ዜናዊ ኢሰባዊ ድርጊቶች፣ ዘረኛና ሽብርተኛ አገዛዝ፣ በኢትዮጵያ አገራችንና በወገኖቻችን ላይ እየፈጸመ ባለው ግፍና በደል የተነሳ፡ የተሰማንን ከፍተኛ ምሬት ለጉባኤው ተሳታፊዎች ለማሰማትና ለአለም ህብረተሰብ ለማጋለጥ ጥሩ አጋጣሚና አስፈላጊ በመሆኑ ሰልፉን ማዘጋጀት ግድ ብሎአል” ብለዋል።

አስተባባሪዎች አያይዘውም “ለአገራችን ህልውና፣ ለህዝባችን መብትና ክብር፣ ለህግ የየበላይነትና እንዲሁም የምናልመውን የዲሞክራሲ ስርአትን እውን ለማድረግ ባካሄዱት ተጋድሎ በወያኔ ቅጥረኞች ታፍነው በየጉድጉዋዱ የሚገኙትን ወ/ት ብርቱካንን ጨምሮ የእልፍ አእላፍ ጀግኖቻችን ነጻነት ለማስጠበቅ እንዲሁም ወገናዊ አጋርነታችንን ለመግለጽ የኢትዮጵያ ደጀን ሆነን በዚህ እለት በአንድነት እንድንቆም ጥሪያችንን እናስተላልፋለን “ ብለዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ዘረኛው መለስ ዜናዊ አፍሪካን ወክሎ በሚሳተፍበት የኮፐን ሀገን ዴንማርክ የአካባቢ ጥበቃ ስብሰባ ላይ የተቃውሞ ሰልፎችን ለማድረግ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን አለማቀፍ ኔት ወርክ ለፍትህና ለዲሞክራሲ በኢትዮጵያ የተባለኔትወርክ ገልጿል። በዲሰምበር 18ና 19 በሚደረገው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ዋና ዋና የሚባሉት የአለም መሪዎች የሚገኙ ሲሆን፣ መለስ ዜናዊን በእነዚህ መሪዎች ፊት ለማጋለጥ ትልቅ እድል ይሰጣል።

መለስ ዜናዊ በተሳሳተ ፖለሲው አገራችንን ወደ መቀመቅ ከከተታት በሁዋላ፣ ማምለጫ ፍለጋ የአየር መዛባትን እንደምክንያት ያቀረበ ሲሆን፣ በዚህ ተንኮሉም የአፍሪካ መሪዎች እርሱን ወክለው ወደ ኮፐን ሀገን እንዲልኩት እድርጎዋቸዋል። መለስ በየትኛውም መስፈርት አፍሪካን ለመወከል የሚያስችል ብቃት እንደሌለው እየታወቀ የአፍሪካ መሪዎች እርሱን በተወያይነት መምረጣቸው በአፍሪካ ውስጥ ምን ያክል ብቃት ያላቸው ሰዎች እየጠፉ እንደሄዱ ያመለክታል የሚሉ አስተያየቶችም በመደመጥ ላይ ናቸው። አንድ አስተያየት ሰጪ ባቀረበው አስተያየት የመለስ ዜናዊ መመረጥ ከዝንጀሮ ቆንጆ የሚለውን ተረት ያስታውሳል ብሎአል።

አምባገነኑ መለስ ዜናዊ በሰብአዊ መብት ጥሰት በአለም ተወዳዳሪ ከሌላቸው አገሮች ተርታ እንደሚመደብ እየታወቀ ፣ ከዲሞክራት መሪዎች ጋር ቁጭ ብሎ ለመደራደር መፈቀዱ በራሱ ጉባኤው ለአፍሪካ ጥያቄ የሰጠውን አነስተኛ ትኩረት ያሳያል የመሉ ወገኖችም አሉ። የኢኮኖሚ እድገት፣ ነጻነት እና የአካባቢ ጥበቃ ተያያዥነት ያላቸው ጽንሰ ሀሳቦች ሆነው ሳለ፣ መለስ ዜናዊ በሚገዛት አገር ውስጥ ሶስቱም ነገሮች የሉም የሚሉት እነዚሁ አስተያየት ሰጪዎች፣ እነዚህን መልካም ነገሮች እንዲጠፉ ያደረገ ሰው እንዴት የአካባቢ ጥበቃ ጠበቃ ሆኖ በአለም መድረክ ፊት ሊቀርብ እንደሚችል አይገባንም ብለዋል።

ግንቦት 7 በውጭ አገር በተለይም በአውሮፓ የሚገኙ አባላትና ደጋፊዎቹ በዚህ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ በነቂስ በመውጣት የመለስ ዜናዊን ዘረኛና አምባገነን አገዛዝ እንዲቃወሙ አሳስቦአል።

## ዶ/ር ነጋሶ አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ይቅርታ . . . ከገጽ 2 የዞረ

የመቻቹ፣ የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱት በህቡና በውጭ አገር የሚንቀሳቀሱት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሀይሎች ጋር ድርድር ይጀምሩ። ይህ ከሆነ ብቻ ነው የምርጫ 97 ስትተት መታረሙንና የሁለት ሺ ሁለት ምርጫ ታማኝነቱ የሚረጋገጠው” ሲሉ ተናግረዋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org ወይም በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661